የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሀያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፭ ቀን ፪ሺ፲፭

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.24
ADDIS ABABA 12th July, 2023

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺/፪ሺ፲፭

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግሥት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ..............................ገጽ ፲፬ሺ፯፻፷፫

## Content

Proclamation No.1290/2023

Mutual Legal Assistance In Criminal Matters Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates Ratification Proclamation.........Page 14763

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺/፪ሺ፲፭

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግሥት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግሥት መካከል በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነት መስከረም ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአቡዳቢ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህኑን ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአካሄደው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO.1290/2023

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE MUTUAL LEGAL ASSISTANCE INCRIMINAL MATTERS TREATY BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE UNITED ARAB EMIRATES**

**WHEREAS** the Mutual Legal Assistance in Crriminal Matters Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates has been signed in Abu Dhabi, on the 21st September, 2022;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Agreement at its session held on 16th Day of May, 2023;

**NOW,THEREFORE**, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግሥት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግሥት መካከል መስከረም ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአቡዳቢ የተፈረመው በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ኃላፊነት</u>**

የኢፌድሪ ፍትሕ ሚኒስቴር ይህን ስምምነት ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ እንዲወስድ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

**፬.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፭ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates Ratification Proclamation No.1290/2023"

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Treaty signed in Abu Dhabi on the 21st September 2022 between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates is hereby ratified.

**3. <u>Responsibility of the FDRE Ministry of Justice</u>**

The FDRE Ministry of Justice is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Treaty.

**4.<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this Day of July 12th, 2023.**

**SAHALE - WORK ZEWEDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**